# Asylum Advice

## የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ



# የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ

## 1.1 ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከት ይፈልጋሉን?

የጥገኝነት ማመልከቻ (ዓለም አቀፋዊ ከለላ) ለማግኘት የሚያመለክቱት ወደ አገርዎት መመለስ የሚያስፈራዎት ከሆነ ብቻ ነው። እ.አ.አ በ1951 በወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን የስደተኝነት ደረጃ ድንጋጌ መሰረት ስደተኛ ለመባል አገርዎን ለቀው መውጣትና በሚከተሉት ምክንያች የተነሳ ህገ ወጥ ጥቃት ወይም በደል ሊፈጸምብዎት እንደሚችል በማስረጃ ማረጋገጥ አለብዎት።

- ዘርዎ
- ኃይማኖት
- ዜግነትዎ
- ፖለቲካዊ አመለካከትዎ ወይም
- የአንድ ማህበራዊ ቡድን አባል መሆንዎ

አቤቱታው ከዚህ በላይ ከተገለጹት አምስት ምክንያቶች አንዱን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ስደተኛ አይደሉም የሚል ውሳኔ ቢተላለፍም እንኳ ወደ ሃገርዎ ቢመለሱ ከባድ ጉዳት ሊደርስብዎት ይችላል ብሎ ለማመን የሚያስችሉ ሌሎች ምክንያቶች ስለሚኖሩ

የሰብዓዊ ጥበቃ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

የዓለም አቀፋዊ ጥበቃ መብትን ይኖረኛል ብለው የማያስቡ ሆነው እያሉ በሌሎች ምክንያቶች አሁንም ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ሊቆዩ ስለሚችሉ የህግ ባለሙያ ምክር ማግኘት አለብዎት።

የዓለም አቀፋዊ ጥበቃ የማግኘት ጥያቄዎዎ ውድቅ ከተደረገ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመቆየትና መጥቶ ጉብኝት ለማድረግ በሚያቀርቧቸው ሌሎች ማመልከቻዎች ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

## 1.2 የጥገኝነት ጥያቄ የማቀርበው የት ነው?

የሚገኙት አውሮፕላን ማረፊያ፣ የባህር ወደብ ወይም ዓለም አቀፋዊ ባቡር ጣቢያ ላይ ነውን?

ጥገኝነት ለመጠየቅ አስበው ከሆነ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) እንደገቡ ወዲያውኑ ጥያቄውን ማቅረብዎ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ከፍርድ ውጭ የሚፈጸም ጥቃትን ሸሽተው ጥበቃና ከለላ የሚፈልጉ ከሆኑ የኢሚግሬሽን ኦፊሰር ማነጋገር እንደሚፈልጉ ያሳውቁ። የኢሚግሬሽን ኦፊሰሩን ሲያነጋግሩ በአደጋ ላይ ስለሚገኙ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ጥገኝነት ለማግኘት ማመልከት እንደሚፈልጉ ማረጋገጥ አለብዎት።

**ቀድሞውኑም የሚገኙት ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ነውን?**

ጥገኝነት መጠየቅ ከፈለጉና የሚገኙትም ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ከሆነ ክሮይደን (ደቡብ ምስራቅ ለንደን) ውስጥ የሚገኘው የጥገኝነት ጉዳይ መነሻ ክፍል ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ ማስያዝ አለብዎት። የጥገኝነት ማመልከቻዎ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ጥገኛ ሰውም ከእርስዎ ጋር መገኘት አለበት።ዩናይትድ ኪንግደም (UK) እንደገቡ ወይም ሁኔታዎችዎ እንደተቀየሩ እንዳወቁ እና ዓለም አቀፋዊ ጥበቃ እንደሚያስፈልጉ እንደተገነዘቡ ወዲያውኑ የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ ጠቃሚ ነገር ነው።

ከቀጠሮ ስርዓት በተጨማሪ የጥገኝነት ጉዳይ መነሻ ክፍልም አልፎ አልፎ ጎራ የሚሉ አመልካቾችን ተቀብሎ ያስተናግዳል። ጎራ በሚሉበት አገልግሎት ከተጠቀሙ በኋላ በተመሳሳይ ቀን ያንኑ አገልግሎት እንደሚያገኙ ምንም ዋስትና እንደሌለዎት እባክዎን ይወቁ።ተመልሰው በመሄድ የቀጠሮ አገልግሎቱን ለመጠቀም መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል በአስቸኳይ። እባክዎት አስተውሉ ወደ Home Office (ሆም ኦፍስ) ለምሄድ የሚያስፈልጎት ለመጉዞ ወደ Croydon (ክሮይዶን) የሚያስፈልጎት ገንዘብ አንከፍልም።

በላይ ከተገለጸው የቀጠሮ አያያዝ መንገድ በላይ የ Asylum Intake Unit (ኣሳይለም ኢንተክ ዩኒት) ቀጠሮ አለመያዝ ወደ ቤትጽሕፈቱ በቐጥታ ለሚመጡ አመልካቶች ሊያስተናግድ ይችላል። ሆኖም ግን  የምታቀርቡት ማመልከቻ በዛን ቀን ሊታይ ይችላል ብለን ልናረጋግጥ ወይም ደግሞ ቃል ንሰጥ አንችልን። ምናልባት ቀጠሮ አድርጋችሁ ለሌላ ቀን እንድትመለሱ ልትጠየቁ ትችላላችሁ።

**የጥገኝነት ጉዳይ መነሻ ክፍል** (Asylum Intake Unit) **ቀጠሮ ስልክ ቁጥር፡** 020 8196 4524

**ቤት ጽሕፈቱ የሚከፈትበት ሰዓት ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከጥዋት** 9፡**ሰዓት እስከ** 4፡30 **ከሰዓት በኃዋላ ሲሆን ዓርብ ከ**9፡00 **ጥዋት እስከ** 4፡15 **ከሰዓት በኅዋላ ነው።**

Asylum Intake (**አሳይለም ኢንይክ**) **የጥገኝነት ጉዳይ ማጣሪያ ክፍል አድራሻ የሚከተለው ነው፡** Lunar House, 40 Wellesley Road, Croydon CR9 2BY
**ቀጠሮዎን መቀየር ወይም መሰረዝ ከፈለጉ እባክዎን በተቻለ ፍጥነት ወደሚከተለው ስልክ ደውለው ያሳውቁ** 020 8196 4524

ሁኔታዎ በቀላሉ አድጋ ውስጥ ሊገቡ የሚችል ሁኔታ ከሆነ በተጨማሪም በ Scotland (ስኮትላንድ) ከሆነ የምትኖሩት የመጀመሪያው ቃለመጠይቅ Screening Interview (ስክሪኒንግ ኢነርቪው) Glasgow (ግላስኮው) ልታደርጉት ሊፈቅድባችሁ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ይህ ውሳኔ በ Home Office (ሆመ ኦፊስ) ነው የሚወሰነው፡ እንደየጉዳዩ አይተው ይሚወስኑት ሁኔታ ነው።

## 1.3 የጥገኝነት ጥያቄና የጥገኝነት ሂደት ላይ የሚሰጥ ምክርና አመራር

የጥገኝነት እርዳታ (Asylum Help) ስደተኞችን የመርዳት በጎ ምግባር (Migrant Help charity) አካል ነው። ድርጅቱ በጥገኝነት እርዳታ (Asylum Help) አማካኝነት ለጥገኝነት አመልካቾች ምክርና አመራር ያለ ምንም ክፍያ ይሰጣል። የጥገኝነት እርዳታ (Asylum Help) ጥገኝነትን በመጠየቅ ላይ፣ በጥገኝነት ሂደት፣ በመኖሪያ ቤት አቅርቦት፣ በፋይናንስ ድጋፍ፣

የህግ አማካሪን በመፈለግ ረገድ፣ በሌሎች የጥገኝነት ጉዳዮች ዙሪያ ነጻ የሆነ ምክር፣ አመራርና መረጃዎችን እርዳታ ይሰጣል።

የጥገኝነት ማጣሪያ ሂደትን የሚመለከቱ፣ የዋና ቃለ መጠይቅና በጉዳይዎ ላይ ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ምን ሊከሰት እንደሚችል ያሉ መረጃዎችን እና ቤት ጽሕፈቱ የሚከፈትበት ሰዓቶች ዩናይትድ ኪንግደም (ASYLUM ADVICE UK) ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ መረጃዎች በ15 ዋነኛ ቋንቋዎች ይገኛሉ። እባክዎ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ www.asylumhelpuk.org.

በቀጥታ አማካሪ ማነጋገር ከፈለጉ እባክዎ ለጥገኝነት እርዳታ መስመር (ምክር) በስልክ ቁጥር 0808 8000 622 ገንዘብ የምይከፈልበት ከ Asylum Advice UK (አሳይለም አፍቫይስ ዩከ) ይደውሉ የጥገኝነት እርዳታ ማእከል የጥገኝነት ማመልከቻዎን በተመለከተ ምንም ዓይነት የህግ ምክር መስጠት እንደማይችል እባክዎን ይወቁ።

## ጥገኝነት ሲጠይቁ የሚካሄድ ነገሮች ሥእል




## 1.4 የጥገኝነት ድጋፍ ይፈልጋሉን?

አቤቱታዎ ከተመዘገበ በኋላ የጥገኝነት ድጋፍ ለማግኘት ካመለከቱ ወይም ቀጠሮ ተሰጥቶዎት ከሆነ ወደሚከተለው የነጻ የስልክ መስመር ይደውሉ፡-

የጥገኝነት እርዳታ መስመር Support Apllication UK (ሳፖርት አፕሊከሽን) (የድጋፍ ማመልከቻዎች) ስልክ ቁጥር 0808 8000 623

አገልግሎቱ በሚረዱት ቋንቋ ሊቀርብልዎት ይችላል።

የጥገኝነት ድጋፍን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎችን የሚያገኙበት ድረ ገጽ፡ www.asylumhelpuk.org

ራስዎን መደገፍ የማይችሉ ቤት አልባ ከሆኑ እባክዎ ይህንን በጥገኝነት የማጣሪያ ሂደት ላይ ግልጽ ማድረግዎን እርግጠኛ ይሁኑ። Home Office ማጣሪያ ከተደረገ በኋላ ወዲያውኑ ሊያቀርብልዎት ለሚችለው ጊዜያዊ ማረፊያ ቤት ያስፈልግዎት እንደሆነ ምርመራ ያደርጋሉ። ወደ እንግሊዝ አገር የመጡት በቪዛ መንገድ ከሆነ ወይም ደግሞ ራስዎን ችሎ እየኖሩ ከቆዩ፡ ስለዚሁ የሚገልጥ መግለጫ እና መረጃ ማቅረብ አለቦት፡ በተጨማሪም አሁን ድሮ የነበሮትን ገቢ ወይም ገንዘብ እንዴት እንደቆመ የሚኣሳይ መግለጫ እና የመጀመሪይ ቃለ መጠይቅ ሲደረግሎት ማቅረብ አለቦት።

በዚሁ ሰዓት በአስቸክዋይ መኖሪያ ቤት እንዲሰጦት ፍቃድ ካልተሰጦት Asylum Help (አሳይለም ሄልፕ) በአስቸክዋይ የመኖሪያ ቤት እርዳታ እንዲሰጦት እርዳታ ሊሰጦት አይችልም፡ ሆኖም ግን የቆዋሚ ለብዙ ጊዜ የሚሆን መኖሪያ ቤት እንዲሰጦት እርዳታ ሊሰጦት ይችላል።

## 1.5 ድጋፍ የሚደረግለት በፈቃደኝነት መመለስ

ጥገኝነት መጠየቅ አልፈልግም ብለው ከወሰኑና ኢመደበኛ ስደተኛ እንደሆኑ በማረጋገጥ ወደ አገርዎ መመለስ ከፈለጉ ከ ስደ Home Office Assisted Voluntary Return ((ሆም ኦፊስ ቮሉንታሪ ረተር ፕሮግራም)

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎት ወደ ኢንተርነት ውስጥ ገብተው በሚቀጥለው አድራሻ ያለው አግለጫ ይመለከቱ።

www.gov.uk/return-home-voluntarily
Voluntary Departures Team: 0300 004 0202

### የዚህን ክፍል ማንኛውም አካልን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ እባክዎ የጥገኝነት ድጋፍን (Asylum Help) ያነጋግሩ

### Asylum Advice UK(አሳይለም አድቫይስ) የጥገኝነት ድጋፍ (ምክር) መስመር 0808 8000 622

### Asylum Support Application UK የጥገኝነት ድጋፍ መስመር (አሳይለም ሳፖርት አፕሊከሽን ዩከ) የጥገኝነት ድጋፍ መስመር (የድጋፍ ማመልከቻዎች) 0808 8000 623